# የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፉፉፌና ማሻሻያ ፕሮጀክቶች እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል የሚደረገው ሽግግር አፈጻጸም በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት





ሚያዚያ 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ



ማውጫ


ክፍል አንድ ........................................................................ 1

መግቢያ ........................................................................ 1

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር ........................ 2

ዓላማ ........................................................................ 2

ሥልጣንና ተግባር ........................................................................ 3

የኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ........................................ 3

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ ምንጭ ........................................................ 4

የኦዲቱ ዓላማ ........................................................................ 4

የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ........................................................ 5

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) ........................................................................ 5

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ ........................................................ 5

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) ................................ 5

የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን ........................................................................ 6

የኦዲቱ ዘዴ ........................................................................ 6

የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description) ........................................ 6

ክፍል ሁለት ........................................................................ 7

ግኝቶች ........................................................................ 7

የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፊያና ማሻሻያ እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚያደርገው የሽግግር ተስማሚ የቴክኖሎጂ መረጣና ዝግጅትን በተመለከተ ................................ 7

የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ መኖሩን በተመለከተ ................................ 9

የፕሮጀክት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ ................................................ 10

የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፋና ማሻሻያ ፕሮጀክቶቹ ስራ በጥናት ላይ የተመሰረተና በተመደበለት በጀትና በኮንትራት ውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ ................ 13

ለፕሮጀክቶቹ  የስራ ተቋራጮችንና አማካሪ ድርጅቶችን መረጣ በተመለከተ ........... 15

የፕሮጀክት ማስፋፊያውንና የሽግግር ፕሮጀክቱን አፈጻጸም ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ ........ 16
የ24 ሰዓት የሥርጭት ሽፋን ማዳረስንና አማራጭ ቻናሎችን መጀመር ተመለከተ ..... 19
ዘመናዊ አርካይቭ ስርዓትና ዳታቤዝ አደረጃጀትን በተመለከተ ........ 21
የምስል፣ የድምፅ ጥራትን በተመለከተ ........ 23
ክፍል ሦስት ........ 25
መደምደሚያ ........ 25
ክፍል አራት ........ 27
የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 27
አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ........ 29
አባሪ 2፡ የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process Description) ........ 31
አባሪ 3፡ ለፕሮጀክት በስራ ላይ የዋለ የገንዘብ መጠን (ከ2000 እስከ 2006 ዓ.ም) ........ 32
አባሪ 4፡ STATUS OF FIRST PHASE PROJECTS ........ 33
አባሪ 5፡ STATUSES OF SECOND PHASE PROJECTS ........ 35

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ሬድዮና ቴሌቪዥን ትልቅ የማስተማሪያ፣ የማሳወቂያ፣ የማዝናኛና የማስተባበሪያ መሳሪያ የሆኑ የብዙሐን መገናኛ ናቸው። በኢትዮጵያ የሬድዮና የቴሌቪዥን አገልግሎት መስጠት የተጀመረው በመጀመሪያ የሬድዮ መገናኛን ለማቋቋም ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ሐምሌ 14 ቀን 1923 ዓ.ም በነፋስ ስልክ ሬድዮ ጣቢያ የመሰረተ ድንጋይ በማኖር ነበር። ከአምስት ዓመት በኃላ የቀድሞው እቴጌ ሆቴል (የአሁኑ ጣይቱ ሆቴል) አጠገብ በነበረው በፖስታ፣ ቴሌግራምና ቴሌፎን መስሪያ ቤት ውስጥ ባለ ሦስት ኪሎ ዋት አጭር ሞገድ ማሠራጫ መሳሪያ ተተክሎ ለአዲስ አበባ ከተማና አካባቢው ሕዝብ የሬዲዮ ዜና ስርጭት ተጀመረ። በ1928 ዓ.ም ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በመውረሩ ጣብያው ወደ ነፋስ ስልክ - አቃቂ-ተዛውሮ በባለ አምስት ኪሎ ዋት ፍራንክን አንቴና በመታገዝ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስለጠላት የግፍ ወረራ ዜና ለዓለም ሕዝብ ያሰራጭ ነበር።

2. የቴሌቪዥንን አገልግሎት ሥራ ምንነትና ጠቀሜታው ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲታወቅ ያደረገው የብሪታንያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (BBC) የተሰኘው የታላቋ ብሪታንያ ኩባንያ በ1948 ዓ.ም የንጉሠ ነገስት ኃይለ ሥላሴ የብር ኢዮቤልዮ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ነበር። የቢቢሲ ቴሌቪዥን ኩባንያ በቴሌኮሙኒኮሽን ፓቪሊዮን ውስጥ ሁለት ካሜራዎችን፣ አራት ሞኒተሮችንና ተጓዳኝ መሳሪያዎች በመጠቀም የቴሌቪዥንን ፕሮግራም ምንነት ለሕብረተሰቡ ያስተዋወቀው። በ1956 ዓ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሀገር ውስጥ መደበኛ ስርጭቱን ጀመረ።

3. የኢትዮጵያ ሬድዮና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ራሳቸውን ችለው ለየብቻቸው አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተው የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን በ1979 ዓ.ም አንድ ላይ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌብዥን ድርጅት /ኤሬቴድ/ በመባል ተዋሃዱ።

4. መንግስት በነደፈው የአምስት ዓመት ዕቅድ መሰረት የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የሚሰጠውን አገልግሎት በዘመናዊ ቴክኖጂና ብቃት ባለው የሰው ኃይል በመታገዝ፣ የስርጭት አድማሱን በመስፋፋት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል። በመሆኑም የተቋሙን አጠቃላይ የማስፈፀም አቅም በመገንባት ፈጠራን፣ ወቅታዊ ግንዛቤን የሚያዳብሩ ጥራት ያላቸውን መረጃዎች በአገር ውስጥና በውጭ ለሚገኙ

ኢትዮጲያውያንና ሌሎች በስፋት በማዳረስ ብሔራዊ መግባባትን መፍጠርና፣ በአፍሪካ ቀንድና በመላው አፍሪካ በመረጃ ስርጭትና በገጽታ ግንባታ ሚና መጫወት፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ አመለካከቶች የሚንሸራሸርበትና ለሕዝብ ተሳትፎ ሰፊ እድል የሚሰጥ የሚዲያ ተቋም እንዲሆን የተለያዩ ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ በዋነኛነት የተያዘው እየተሰራበት ካለው የአናሎግ ቴክኖሎጂ ወደ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ማሸጋገር ነው፡፡ ይህን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ከ 2000 — 2006 ዓ.ም በሁለት ዙር (ፌዝ) የሚጠናቀቅ ፕሮጀክት ተቀርጾና ብር 2,372,496,798.00 (ሁለት ቢሊዮን ሦስት መቶ ሰባ ሁለት ሚሊዮን አራ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ብር) ለፕሮጀክቱ በማስፈቀድ ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ሽግግር ፕሮጀክቶችን የግንባታ ሥራን እየተከናወነ ይገኛል፡፡

5. የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት መንግሥትና ሕዝብን በማገናኘት የሕዝቡን የልማት ተሳታፊነትና የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚጠበቅበትን ሚና በአግባቡ መወጣት እንዲችል እና በህብረተሰቡ መካከል ሐሳቦችና አመለካከቶች በሕገመንግሥቱ በተደነገገው መሠረት በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ የተቋምና የአሠራር ነፃነት እንዲሁም የተሻለ የሕግ ጥበቃ እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ እና የብሮድካስት አገልግሎት ቴክኖሎጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየተሻሻለ በመምጣቱ ይህንኑ ባግባቡ ተጠቅሞ የሕዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ያለውን የብሮድካስት አገልግሎት አደረጃጀትና አሠራር ማሻሻል በማስፈለጉ፤ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 858/2006 ተብሎ እንደ አዲስ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

## የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር

### ዓላማ

6. በአዋጅ ቁጥር 858/2006 መሰረት ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉት አላማዎች አሉት እነርሱም፡-

- በመገናኛ ብዙሃንና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎችና ፖሊሲዎች መሠረት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ስለሚፈጸሙ አበይትና ወቅታዊ ጉዳዮች እንዲሁም ትምህርታዊና አዝናኝ ዝግጅቶችን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በድረ-ገጽ በማቅረብ፣ ከሕዝቡም በግብረ-መልስ ሥርዓት ወይም በቀጥታ የሚገኘውን ግብዓት በመጠቀም ሕዝቡ በሀገሪቱ በሚካሄዱ ሁለንናዊ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ኖሮት በሀገር ልማት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ፤

- ብሔራዊ መግባባት በመፍጠር ሀገራዊ ማንነትን፣ ብዝሃነትን፣ መቻቻልንና ዲሞክራሲያዊ አንድነትን ለመጠበቅና ለማጎልበት የሚደረገውን ሀገራዊ ጥረት ማገዝ፣

ናቸው፡፡

## ሥልጣንና ተግባር

7. ድርጅቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-
    - ለሕዝብ ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑ ዜናዎችና መዋዕለ-ዜናዎችን ማሰባሰብ፣ ማዘጋጀትና በሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና በድረ-ገጽ በልዩልዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ቋንቋዎች በማሠራጨት ለተገልጋዩ የማድረስ፤
    - ለልማት፣ ለመልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ ግንባታ ህብረተሰቡን የሚያነሳሱ ትምህርታዊና አሳዋቂ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤ የመንግስትን ፖሊሲዎችና ሕጎች ለሕዝብ የማስተዋወቅ፣
    - ሕዝቡ ስለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር የሚረዱ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣
    - ነፃ የህዝብ አስተያየቶችንና ጥቆማዎችን ተቀብሎ የማስተላለፍ፤
    - የሕዝቡን ዕውቀትና ፈጠራ የሚያዳብሩና የመዝናናት ፍላጎቱን የሚያረኩ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣
    - በሀገር ውስጥና ከውጭ ካሉ ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት የመመሥረት፣
    - ለክልል ብዙሃን መገናኛ ድርጅቶች የቴክኒክና የሥልጠና ድጋፍ የመስጠት፣
    - ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ የመወሰንና የመሰብሰብ፣ እንደ አስፈላጊነቱ በከፊል ወይም በሙሉ ከክፍያ ነፃ የማድረግ፣
    - የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤
    - ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን የማከናወን፡፡

## የኮርፖሬሽን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

8. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ተጠሪነቱ ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሆኖ በአንድ(1) ዋና ዳይሬክተር በአጠቃላይ በድርጅቱ ሥር 5 (አምስት) ወሳኝ የስራ ሂደቶች 7 (በሰባት) ደጋፊ በድምሩ በ11 የሥራ ሂደቶች ተዋቅረዋል፡፡ ዋና ዳይሬክተሩ አጠቃላይ በፖሊሲና እስትራቴጂክ አካሄድ ላይ ተመስርቶ በበላይነት የመምራትና

የማቀናጀት፣ የማስተባበርና የመቆጣጠር ተግባር ይዞ ለሁሉም የስራ ሂደት ባለቤቶች ሙሉ የሥልጣን ውክልና በመስጠት ሥራው እየተከናወነ ይገኛል፡፡

## የሰው ኃይል

9. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን አደረጃጀትና የሰው ኃይል በትምህርት በአሁኑ ወቅት ለእነዚህ የሥራ ሒደቶች በመሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ ጥናት (BPR) መሠረት በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል ብዛት 2101 ሲሆን፡፡ ይህም በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ሁለተኛ በድግሪ 40፤ መጀመሪያ ድግሪ 482፤ ዲፕሎማ 709፤ ሰርተፍኬት 75፤ 12ኛ ክፍል 124፤ ከ12ኛ ክፍል በታች 671 ሰራተኞች ሲሆኑ በጾታ ሲገለፅ ወንድ 1474 ሴት 627 ናቸው፡፡

## የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ ምንጭ

10. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ስራውን እያከናወነ ያለው በመንግስት በሚመደብለት በጀት እና ከውስጥ ከሚሰበሰብ ገቢ (ከተለያዩ ከማስታወቂያ፣ ከስፖንሰር ሺኘ፣ ከአየር ሰዓት ሽያጭ፣ ከሀብት ኪራይ፤ ከSMS መልዕክት፣ ከዶክመንታሪ ሥራ፣ ከትምህርትና ሥልጠና፣ ከቴክኒክ አገልግሎት ገቢ) ከሚሰበሰበው የውስጥ ገቢ ነው፡፡ ለኮርፖሬሽኑ (ለቀድሞው ኢሬቴድ) ለመደበኛ በጀት እና ለካፒታል በጀት በድምሩ በ2003፣ በ2004፣ በ2005 እና 2006 በጀት ዓመታት እንደ የቅደም ተከተሉ የተመደበለት ብር 795,571,100፤ 1,080,226,600፤ 931,688,750 እና 607,572,900 ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ2003 በጀት ዓመት ብር 835,522,524፤ በ2004 በጀት ዓመት ብር 960,896,935፤ በ2005 በጀት ዓመት ብር 591,888,583 እንዲሁም በ2006 በጀት ዓመት ደግሞ ብር 327,924,958 ስራ ላይ ውሏል፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲነግ ኮርፖሬሽን የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቶች እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ሽግግር አፈጻጸምን በቁጠባ፤ በብቃት እና በስኬታማነት ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን፤ በዚህ ዙሪያ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ወይም የአሰራር ግድፈቶችን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

12. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ***"የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን*** የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቶች እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ሽግግር ***አፈጻጸም በተመለከተ የዘረጋው የአሠራር ስርዓት በቁጠባ፤ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም"*** የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

### የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ

13. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ሥር ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ተመርጠዋል፡፡ እነሱም፡-

1. የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቶች እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚደረገው የቴክኖሎጂ ሽግግር ፕሮጀክቶች ወጥነት ባለው የቅድመ ትግበራ ግምገማ፤ የሥራ አፈጻጸም ክትትል ስርዓት እና የድህረ ትግበራ ግምገማ የሚከናወን መሆኑን መገምገም ::
2. የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቶች እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል የቴክኖሎጂ ሽግግር ፕሮጀክት ዝግጅት ጥናት ሥራ፣ ለዲዛይን፣ ቁጥጥርና ለሌሎች ማናቸውም ተያያዥ ሥራዎች አገልግሎት የሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎችን መረጣ፣ የኮንትራት አስተዳደር፣ ርክክብ እና የክፍያ አፈጻጸም የመንግስት የግዥ ደንብ፣ መመሪያ እና ማንዋል መሠረት ተከትሎ መፈጸሙን ማጣራት

ናቸው፡፡

### የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

14. ከላይ የተመረጡት ሁለት የኦዲት ጭብጦችን (Audit Issues) ለመመዘን የሚረዱ 29 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑ የድርጅቱ መቋቋሚያ አዋጅ፣ ስትራቴጂክ ዕቅዶች፣ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን፣ የሥራ መመሪያ እና በድርጅቱ የተጠናው መሰረታዊ የስራ ሒደት ለውጥ ጥናቶች፣ መልካም ተሞክሮዎች፣ የሥራ አመራር ቃለ ጉባኤዎች

እና የዳሬክተሮች ቦርድ ቃለ ጉባኤዎችን ሲሆኑ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ሥራው የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) **በአባሪ 1** ተያይዟል፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን

14. ዝርዝር ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2001 የበጀት ዓመት እስከ 2006 በጀት ዓመት ድረስ ያለውን የኢትዮጵያ ብሮድካስቲነግ ኮርፖሬሽን ወደ ዲጂታል ሽግግር የፕሮጀክቶች የግንባታ አፈጻጸም የሥራ ክንውን እና ፕሮጀክቶቹ ከተጀመሩ ጊዜ ጀምሮ ያሉ ጉልህ ጉዳዮች ነው፡፡ ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (የቀድሞው ኢሬቴድ) ዋና መስሪያ ቤት ለሚዲያ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት፤ ለትራንስሚተር ዳይሬክቶሬት እና በናሙና በተመረጡ ዘጠኝ ቅርንጫፍ የግንባታ ጣቢያ ሲሆን፤እንዲሁም ዋነኛ ባለድርሻ አካላት ከሆኑ የስራ ተቋራጮች እና አማካሪ መሃንዲሶች በኦዲቱ ተካተው ታይተዋል፡፡

## የኦዲቱ ዘዴ

15. ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር መጠይቅ በማድረግ፣ የተለያዩ ዶክመንቶችን በመከለስ ሲሆን በተጨማሪም ኦዲቱ በናሙና በተመረጡ በአዳማ (ናዝሬት)፤ ድሬዳዋ፤ ደሴ፤ ወልዲያ፤ ባህር ዳር፤ ጮቄ፤ ፊቼ፤ ከሚሴ እና ሂርና በቅርንጫፍ ማሰራጫ ጣቢያዎች በአካል በመገኘት ለጣቢያ ኃላፊዎች መጠይቅ በማድረግ እና ነቀምት፤ ቦንጋ፤ ሀረር እና አመንቲላ በቅርንጫፍ ማሰራጫ ጣቢያዎች መጠይቅ በመላክ እና የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ በተሰበሰቡት ማስረጃዎች ላይም አስፈላጊውን ትንተናና ንፅፅር (Analysis) በማካሄድ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## የሥራ ሂደት መግለጫ (Process Description)

16. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካትና አለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የሚዲያ ተቋም እንዲሆን ይረዳኛል ያለውን የአሰራር ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ የአሰራር ሥርዓቱ (Process Description) ስዕላዊ መግለጫ **በአባሪ 2** ይመልከቱ፡፡

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፊያና ማሻሻያ እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚያደርገው የሽግግር ተስማሚ የቴክኖሎጂ መረጣና ዝግጅትን በተመለከተ

17. የሬዲዮና የቴሌቪዥን ማፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጄክትና እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚያደርገው ሽግግር ተስማሚ የቴክኖሎጂ መረጣ ለማካሄድ የሚያስችል መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለሚደረገው የቴክኖሎጂ ሽግግር ፕሮጀክት ዝርዝር የግንባታ ዲዛይን ጥናት ሊከናውንና በጥናቱም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

18. ኮርፖሬሽኑ (የቀድሞው ኢሬቴድ) የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎት የሚስፋፋበትንና በተስማሚ ቴክኖሎጂ የሚደራጁበትን ሁኔታ በማጥናት፤ መስፈርቶችን በማዘጋጀት ሐሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ማዋል እንዳለበት በመቋቋሚያ አዋጁ የተቀመጠ ቢሆንም የሬዲዮና የቴሌቪዥን ማፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ ተስማሚ ቴክኖሎጂ መረጣ ለማካሄድ የሚያስችል የመምረጫ መስፈርት በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በኩል መከናወኑን ታውቋል፡፡

19. ይሁን እንጂ የመሳሪያ ተከላ ቦታ መረጣን በተመለከተ በኦዲቱ ውቅት በናሙና ከታዩት ማሰራጫ ጣቢያዎች ውስጥ ፡-
    - በድሬዳዋ የቴሌቪዥን ማሰራጫ ጣቢያ ጽ/ቤትና የማሰራጫ ትራንስሚሽን የተገነባበት ቦታ የሲሚንቶ ፋብሪካ የጥሬ ዕቃ ማመረቻ ክልል ውስጥ መሆኑን፣ የጣቢያ መስታዎቶቹ ከመሰባበራቸውም ባሻገር ጽ/ቤቱ ግድግዳ በመሰነጣጠቅ ዝናብ እያስገባ በማሽኖች ላይ ጉዳት እያደረሰ መሆኑን፣
    - የደሴ የቴሌቪዥን ማሰራጫ ጣቢያ የተገነባበት ቦታ ለመድረስ የሚያስችል መንገድ አለመሰራቱ፤
    - የጮቄ ተራራ ማሰራጫ ጣቢያ የተገነባበት ቦታ ከደብረ ማርቆስ ከተማ በ50 ኪሎ ሜትር የሚርቅ መሆኑና የማብራት አገልግሎት የሌለው በመሆኑ ለጀኔሬተር የሚያስፈልገው ነዳጅ ለማጓጓዝ እና ብልሽት በሚከሰትበት ወቅት የጥገና ባለሞያዎች (ቴክኒሺያኖችን) ወደ ቦታው ሄደው ችግሩ በወቅቱ

እንዲስተካካል ለማድረግ የሚያስችል የተመደበ የትራንስፖርት አገልግሎት አለመኖሩን ለማወቅ ተችላል፡፡

20. ለዲጅታል ሽግግሩ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቴክኖሎጂን በተመለከተ ደግሞ፡-

- ለዲጂታል ሽግግሩ ከሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች መካከል በማስፋፊያ እና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ Ultra High Frequency (UHF[1]) ፍሪክዌንሲ ሬንጅ የተሰሩ Dual cast[2] (አናሎግ እና ዲጂታል ሲግናሎችን እያፈራረቀ የማሰራጨት አቅም ያላቸው) (73) ሰባ ሦስት የቴሌቪዥን ትራንስሚተሮች ተከላቸው የተጠናቀቀ ቢሆንም፤ ኮርፖሬሽኑ (የቀድሞው ኢሬቴድ) የማሻሻያ እና ማስፋፊያ ፕሮጀክቱን ከማከናወኑ በፊት ይጠቀምባቸው ከነበሩት ሠላሳ አንድ (31) ትራንስሚተሮች በVery High Frequency (VHF[3]) ሬንጅ ከሚሰሩት ውስጥ አምስቱ (5) የማሻሻያ ስራ ተከነውኖባቸው (UHF) አገልጎሎት መስጠት እንዲችሉ ተደርጓል፡፡

21. ይህን በተመለከተ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ለሚያደርገው የሽግግር ፕሮጀክት የቴክኖሎጂ መረጣ ለማካሄድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት በድርጅቱ አለመኖሩን ለጊዜው ግን በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ በኩል የቴክኖሎጂ መረጣው ጥናት እንዲጠና የተደረ መሆኑ፤ የድሬዳዋ ቴሌቪዥን መሰራጫ ጣቢያ የተገነባበት ቦታ የሲሚንቶ ድንጋይ ማምረቻ አለመሆኑና አንድ ጊዜ ለሙከራ በፈነዳ ድማሚት መስታወቱ ጉዳት እንደደረሰበት ከዛ ቦኃላ ግን ድርጊቱ እንዲቆም ለድርጅቱ በ07/10/2005 ደብዳቤ የተጻፈ መሆኑን፤ የደሴ ቴሌቪዥን ማሰራጫ ጣቢያ በማስፋፊያና መሻሻያ ትግበራ ወቅት መንገዱ በአማራ የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን የተሰራና በኋላ በጎርፍ የተበላሸ መሆኑ፤ የጮቄ ተራራ ቴሌቪዥን ማሰራጫ ጣቢያ ደግሞ በተቋሙ የተመደበ መኪና የነበረውና በብልሽት ምክንያት ወደ ዋናው መ/ቤት እንደመጣ እና የ26ቱ አናሎግ ብቻ ማሰራጨት የሚችሉ ትራንስሚተሮች ከሽግግሩ በኋላ የሚኖራቸው ቀጣይ ዕጣ ፈንታ ወደፊት የሚታይ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ የዲጂታላይዜሽን ሽግግር ፕሮጀክትን ተግባራዊ ለማድረግ የቀድሞው ኤሬቴድ ጥያቄ ፕሮጄክቱ በከፍተኛ ደረጃ የሚመራና የሚከታተል ብሔራዊ ስትሪንግ ኮሚቴ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተቋቋመ በመሆኑ ኮርፖሬሽኑን እንደማይመለከተው ገልጸዋል፡፡

---

[1] UH F ምስል እና ድምጽ የሚተላለፍበት እጅግ በጣም ከፍተኛ የሬዲዮ ሞገድ (300MHz- 3000MHZ)

[2] Dual cast አናሎግ እና ዲጂታል ሲግናሎችን እያፈራረቀ ማስተላለፍ የሚችል ማሠራጫ መሣሪያ

[3] VH F ምስል እና ድምጽ የሚተላለፍበት በጣም ከፍተኛ የሬዲዮ ሞገድ (30MHz- 300MHZ)

22. የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ጣቢያዎች የተተከሉበት ሥፍራ ለሥርጭት አመቺ ሊሆኑ ቢችሉም በተጨባጭ ግን በናሙና በታዩት ማሰራጫ ጣቢያዎች ግድግዳ በመሰነጣጠቅ ዝናብ እያስገባ በማሽኖች ላይ ጉዳት እያደረሰ መሆኑ፤ ወደ ጣቢያ የሚወስድ መንገድ አለመኖር፤ የጀኔሬተር ነዳጅ፤ ጣቢያው ብልሽት ቢገጥመው ለመጥገንና ክትትል ለማድረግ የሚያስችልቀ ተሽከርካሪ አለመኖር እና የ26ቱ አናሎግ ብቻ ማሰራጨት የሚችሉ ትራንስሚሽኖች የሽግግሩ አካል እንዲሆኑ አለመደረጋቸው በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ችሏል፡፡ በተጨማሪም የዲጂታላይዜሽን ሽግግር ኮርፖሬሽኑን አይመለከተውም ይበሉ እንጂ ሥራው በቀድሞው ኢሬቴድ የስትራቴጂክ እቅድ የተያዘና በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ጠ80-አጠ7/08/72 በየካቲት 30 2003 የተቋቋመው ብሔራዊ ስትሪንግ ኮሚቴ ድርሻ ኤሬቴድ እያጠና ለሚያቀርባቸው የፖሊሲና የአቅጣጫ ጉዳዮች እንዲወስን ለማድረግ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ እንዳለ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

## የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ መኖሩን በተመለከተ

23. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ለማስፋፊያ ፕሮጀክቱ የቴክኖሎጂ ተከላ፤ የዕቃ አቅርቦት፤ የሲቪል ግንባታና የኮሚሽኒግ ሥራ ለመከታተልና ለማቆጣጠር የሚያስችል የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) የመንግስትና የድርጅቱን የፕሮጀክቶች አዘገጃጀት መመሪያን መሰረት አድርጎ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

24. በኦዲቱ ወቅት ኮርፖሬሽኑ (የቀድሞው ኤሬቴድ) የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ለፕሮጀክቱ የቴክኖሎጂ ተከላ፤ የዕቃ አቅርቦት፤ የሲቪል ግንባታና የኮሚሽኒግ ሥራ ለመከታተልና ለማቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር መመሪያ በኮርፖሬሽኑ ያልተዘጋጀ መሆኑን ከተከለሱ ዶክመንቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡ መመሪያ ተዘጋጅቶ ክትትል ባለመደረጉ የጣቢያ ግንባታቸው ርክክብ ከተፈፀመባቸው በኂላ በብልሽት ላይ መሆናቸውን የኦዲት ቡድኑ በመስክ ጉብኝት በናሙና ከታዩት ዘጠኝ (9) የማሰራጫ ጣቢዎች ውስጥ አምስቱ (5) ግንባታቸው በመሰነጣጠቅ በክረምት ዝናብ በማስገት በመሳሪያዎቹን ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

25. ስለሁኔታው የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ የፕሮጀክት ጽ/ቤት በወቅቱ የፕሮጀክት ጽ/ቤቱን ለመቋቋም የሚስፈልገውን ሰው ኃይል፣ ደመወዝና የገንዘብ ፍላጎት ጥያቄ ለሥራ አመራራ ቦርዱ ቀርቦ በራስ ኃይል በሚዲያ ቴክኖሎጂ ማስፋፋያ የስራ ሂደት ባለቤትነት

እንዲሰራ የተወሰነ በመሆኑ ጽ/ቤቱ እንዳልተቋቋመ ገልጸዋል፡፡ የአሰራር መመሪያን በተመለከተም የመንግስት የፋይናንስ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር መመሪያን እንዲሁም የኮንስትራክሽን አሰራር መመሪያን መሰረት አድርጎ ስራዎች እንዲሰሩ ተደርጓል ብለዋል፡፡ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የተባሉትን መመሪያዎች መሰረት በማድረግ የሚዲያ ቴክኖሎጂ የሥራ ሂደት ሥራውን ባለመፈጸሙና ፕሮጀክቱን የሚመለከቱ የተሟላ ሰነዶች በሥራ ሂደቱ ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡




*ሥዕል፡-* ግንባታቸው በመስነጣጠቅ ለብልሽት ከተዳረጉትና ዝናብ በማስገባት ከሚገኙት ጮቂ ተራራና ድሬዳዋ ማሰራጫ ጣቢያዎች በከፊል

## የፕሮጀክት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ

26. አገር አቀፍ የራዲዮና የቴሌቭዥን የማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክት በተቀመጠለት ጊዜ በዕቅዱ መሰረት ተጠናቆ ሥራ ሊጀምር ይገባዋል፡፡

27. በ2001 ዓ.ም አገር አቀፍ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ለማስፋፊያ እና ማሻሻያ ኘሮጀክቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የመሣሪያ ግዥውና የህንፃ ግንባታው ተጠናቆ ማሠራጫ መሣሪያዎቹን በመትከል ሥርጭት ይጀምራል የሚል ለፕሮጀክቱ በፀደቀ የጥናት ፕሮፖዛል ላይ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም በማስፋፊያና ማሻሻያ ኘሮጀክት ጥናት ፕሮፖዛል እና በ5 ዓመቱ (2003-2007) ስትራቴጂክ ዕቅድ ትራንስሚተሮች ተከላ ሥራ እስከ 2004 ዓ.ም ተግባራዊ በማድረግ የሬዲዮን ከ75% ወደ

95% የቴሌቪዥን ከ55% ወደ 86% ሽፋን በላይ ማድረስ እና የዲጂታል ስርጭት በየካቲት 2005 ዓ.ም ይጀምራል የሚል ቢሆንም አፈጻጸሙ ግን በዕቅዱ ከተጠቀሰው በሁለት ዓመት የዘገየ መሆኑ እና በአዲቱ ወቅትም የአንድ (ደርባ) ማሰራጫ ጣቢያ የትራንስሚሽን ግንባታና ተከላ ያልተጀመረ መሆኑን ከዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. የዲጂታል ስርጭትን ለማካሄድ የዲጂታል ማሰራጫ መሳሪያ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ለመቀበያም አስፈላጊ የዲጂታል ስርጭት የመቀበያ መሳሪያዎች ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም የዲጂታል መቀበያ መሳሪያዎች በዋነኝነት ሴት-ቶፕ ቦክስ፣ ዲጂታል ቴሌቪዥን (DTV[4]) እና UHF አንቴና ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን እና የቴሌቪዥን ማሠራጫ ጣቢያዎች ለዲጂታል ሥርጭት ወደ DVB- T2 (Digital video Broadcasting Terrestrial 2nd generation) የመቀየር ሥራ፤ የSet Top Box[5] (የዲጂታል ቴሌቪዥን ትራንስሚሽንን ለማየት ከቴሌቪዥን ጋር የሚገጠመው ዲኮደር)፤ የትራንስሚተር አፕግሬድ (Transmitter Up Grading) እና የሄድ ኢንድ (Head End) ሥራ በተመለከተ በ2005 ዓ.ም የሚጠናቀቅ መሆኑ በሽግግር ፍኖተ ካርታ (ሮድማፕ) ሰነዱ እና ስትራቴጂክ ዕቅድ የተገለጸ ቢሆንም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ስራው ያልተጀመረና ያልተጠናቀቀ መሆኑን ከዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ታውቋል፡፡

29. በተጨማሪም ለዲጂታላይዜሽን የሚያገለግለው UHF የቴሌቪዥን አንቴናዎች በሀገር ውስጥ ገበያ በብዛት አለመኖርና ስለአንቴናው አስፈላጊነት ለህብረተሰቡ አስፈላጊውን ግንዛቤ የመፍጠር ስራ አለመከናወኑ እና አሁንም ድረስ VHF አንቴናዎች በገበያው ውስጥ መሆናቸው ለዲጂታላይዜሽን ሽግግሩ ተግባራ ተግዳሮት ፈጥሯል፡፡ የሴት ቦክስ አቅርቦትና ስርጭትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሮድካት ባለስልጣን የአምራቾችና አስመጪዎችን ዝርዝር መስፈርት በማዘጋጀትና በመምረጥ እና የማረጋገጫ ሠርተፍኬት በመስጠት እንዲሁም ከዚሁ ጋር የተያያዘ የቁጥጥሩን ስራ እንዲከናውን በቁጥር 001/901/01 በ28/05/07 የዲጂታላይዜሽን ትግበራ ስትሪንግ ኮሚቴ ለባለስልጣኑ ማሳወቁን ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

30. ስለሁኔታው የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ለማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቶች በወቅቱ አለመጠናቀቅ እና በዕቅድ

---

[4] DVB-T2 የዲጂታል ቪዲዮ ብሮድካስት ቴሬስቴሪያል የስርጭት ስታንዳርድን የተለያዩ ቴክኒካዊ ባህርያትን በማሻሻል አፈጻጸሙን ከ50 ፐርሰንት በላይ ያሻሻለ ሁለተኛው የስርጭት ስታንዳርድ

5 Set Top Box የአናሎግ ስርጭት እንዲቀበሉ ተደርገው የተሰሩት የቴሌቪዥን መቀበያዎች ጋር በመያያዝ የዲጂታል ስርጭትን እንዲቀበሉ የሚያደርግ መሳሪያ

ከተቀመጠላቸው ጊዜ በላይ መውሰድ ተጠቃሽ ከሆኑ ምክንያቶች ውስጥ የማሰራጫ ጣቢያዎቹ የሚተከሉባቸው ቦታዎች ይዞታ ለማስፈቀድ የነበረው ሂደት እጅግ መርዘም፣ ከፍተኛ የግንባታ ግብዓቶችና የባለሙያ እጥረት፣ በግንባታ ቦታዎች ላይ ያለው አስቸጋሪ የሆነ የአየር ንብረትና የክረምት ሁኔታ፣ የግንባታ ቦታዎች እርቀትና ለስራ አዳጋች የሆነ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ፣ የታወር ብረቶች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና እና ወደ ጣቢያዎቹ ለማጓጓዝ የፈጀው እረጅም ጊዜ እንዲሁም የተወሰኑ ተቋራጮች ደካማ የስራ አፈፃፀም ማሳየት ዋነኞቹ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በውለታቸው መሰረት ሥራቸውን አጠናቀው ባላስረከቡት ላይ ኮርፖሬሽኑ አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ የዲጂታላይዜሽን ሽግግር ፕሮጀክትን ተግባራዊ ለማድረግ የቀድሞው ኤሬቴድ ጥያቄ ፕሮጀክቱ በከፍተኛ ደረጃ የሚመራና የሚከታተል የስትሪንግ ኮሚቴ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተቋቋመ በመሆኑ ኮርፖሬሽኑን እንደማይመለከተው ገልጸዋል፡፡ የዲጂታላይዜሽን ሽግግር ኮርፖሬሽኑን አይመለከተውም ይበሉ እንጂ የተቋቋመው የስትሪንግ ኮሚቴ ድርሻ ኮርፖሬሽኑ (የቀድሞው ኢሬቴድ) እያጠና ለሚያቀርባቸው የፖሊሲና የአቅጣጫ ጉዳዮች ላይ እንዲወስን ለማድረግ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡

31. በአጠቃላይ ኮርፖሬሽኑ በዕቅድና በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ለፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም አስፈላጊ ዝግጅት ባለመደረጉና ለዲጂታል ሽግግሩ ከሚያስፈልጉ ባለድርሻ አካለት ጋር በቅንጅት አለመተግበሩ የዕቅድን አፈጻጸሙን ዝቅተኛ እንዲሆን ከማድረጉም ባሻገር ኮርፖሬሽኑ የተቋሙን ሥራዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት እንዲጓተት ከማድረጉም በላይ ኮርፖሬሽኑ የሬዲዮን ከ75% ወደ 95% የቴሌቪዥን ከ55% ወደ 86% ሽፋን በተጠቀሰው አሀዝ አድርሻለሁ ቢልም የፕሮጀክቱ አካል የሆነው ወደ 46% የሚሆነው የጽ/ቤት ግንባታ በተቀመጠለት መስፈርት መሰረት ተገንብተው ያልተጠናቀቁና ርክክብ ያልተፈጸሙባቸው በመሆኑና ቴክኖሎጂውን በመረጃ ተጠቃሚው ክፍልና ለአጠቃላዩ ህብረተሰብ ማስተዋወቅ፣ ቴክኖሎጂው ለኢኮኖሚ ልማት መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠርና ስርዓቱን ማጠናከር፣ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ የትብብር ፕሮግራሞችን መመስረትና ማስፋፋት ስራዎች አለመከናወናቸውን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

## የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፋና ማሻሻያ ፕሮጀክቶቹ ስራ በጥናት ላይ የተመሰረተና በተመደበለት በጀትና በኮንትራት ውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ

32. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የተደራሽነት አድማሱን ለማስፋትና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚያደርገው ሽግግር የተዘጋጀው የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክት በበቂ ጥናት ላይ ሊመሰረት ይገባል፡፡ ሮጀክቱን የሚያከናውነው የስራ ተቋራጭ በኮንትራት ውሉ በተቀመጠለት የገንዘብ መጠን መሰረት ማከናወን እና ተፈጻሚ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

33. የተቀናጀ የክትትልና ቁጥጥር የአሰራርና አደረጃጀት ሥርዓት በመፍጠር የፅ/ቤት የግንባታውን ሥራ በሁለት ዙር በሦስት ዓመታት ለመጀመሪያው ዙር (1st phase) የካቲት 2001 - ሐምሌ 2003 ዓ.ም ሲሆን ለሁለተኛው ዙር (2nd phase) ከጥቅምት 2002 - ሰኔ 2004 ዓ.ም ጊዜ ውስጥ የፅ/ቤት የግንባታውን በማጠናቀቅ ወደ ቴክኖሎጂ ገጠማው ይገባል በሚልይ ቢሆንም፡፡ በተግባር ግን የፅ/ቤት ግንባታው ፕሮጀክት በኮንትራት ውሉ ከተቀመጠው ከሁለት ዓመት በላይ የወሰደ መሆኑ ከኮንትራት ውሉ እና ከፕሮጀክቱ አፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. የፕሮጀክት ጥናቱ የመሳሪያ ግዥ፣ ተከላ እና የግንባታ ወጪዎችን በቻ ያስቀመጠ ሲሆን ሌሎች ወጪዎች በትናቱ ልተካተቱ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚያደርገው የሽግግር ስራ በሁለቱም ዙር (1st phase እና 2nd phase) የትራንስሚሽን ቴክኖሎጂ ግዥና ገጠማው፤ ዲጂታል ስትዲዮና ተጓዳኝ ስራዎቸ በብር 1,098,456,410 (አንድ ቢሊዮን ዘጠና ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ አስር ብር) እና ለ74 ጣቢያ ግንባታዎች ግንባታ ብር 410,471,550 (አራት መቶ አሰር ሚሊዮን አራት መቶ ሠባ አንድ ሺ አምስት መቶ ሀምሳ) እንደሚጠናቀቅ የተገለጸ ሲሆን ነገር ግን ሌሎች ዋና ዋና ወጪዎች (የመርከብ፣ የአውሮፕላን፣ ከወደብ ወደ መሃል አገር ለመጓጓዝ የማጓጓዣ፣ ለጉምሩክ ቀረጥ፣ የአማካሪ ክፍያ…ወዘተ) ወጪዎችን በፕሮጀክት ጥናቱ ውስጥ ባለመካተታቸው ከ2000-2006 ዓ.ም ለፕሮጀክቱ በሁለቱም ዙር በስራ ላይ የዋለ የገንዘብ መጠን ብር 1,740,552,471 (አንድ ቢሊዮን ሠባት መቶ አርባ ሚሊዮን አምስት መቶ ሀምሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ ሠባ አንድ ብር) በመሆኑ በፕሮጀክት ጥናቱ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በላይ ብር 642,096,007 (ስድስት መቶ አርባ ሁለት ሚሊዮን ዘጠና ስድት ሺህ ሠባት ብር) 58% ወጪ የተደረገ ሲሆን ለፅ/ቤት

ግንባታው ፕሮጀክት ደግሞ 365,941,046 (ሦስት መቶ ስልሳ አምስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አርባ አንድ ሺ አርባ ስድስት) ወጪ የተደረገ መሆኑን ከፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ከቀረበ የሰነድ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል **አባሪ 3** ይመልከቱ፡፡

35. ይህ በተመለከተ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በመጠይቅ፣ በነባረዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የተቋራጮች አቅም ውስንነት፤ ኮንሰልታንቱ ለስራው ያለው ሱፐርቭዥን ዝቅተኛ መሆን የተቀናጀ እና የተጠናከረ የተከላ ስራ አለመኖር፤ ተቋራጮች ስራውን በዕቅድ ባለመመራታቸውና ክትትል እና ቁጥጥር ባለማድረጋቸው ለፕሮጀክቶቹ መጓተት ትልቁን ሚና መጫወቱንና የገንዘብ ጭማሪው ግን የግንባታና የመሳሪያ ግዥ ወጪን ብቻ ያካተተ እንጂ ከስራው ጋር ተያያዝ የሆኑ (የምንዛሬ ለውጥ፣ የመርከብ፣ የአውሮፕላን፣ ከወደብ ወደ መሃል አገር ለመጓጓዝ የማጓጓዣ፣ ለጉምሩክ ቀረጥ፣ የአማካሪ ክፍያ…ወዘተ) ወጪዎችን በፕሮጀክት ጥናቱ ውስጥ ያልተካተቱ መሆኑና ፕሮጀክቱ ሲጀመር የነበረው የዶላር ምንዛሬ ፕሮጀክቱ ከተጀመረ በኂላ ጭማሪ በማሳየቱ የተከሰተ ልዩነት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጀ አንድ ፕሮጀክት ሲታቀድ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ወጪዎች ሁሉ ከግምት ውስጥ በመግባት ከፕሮጀክቱ በጀት ጋር መካተት የነበረበትና አፈጻጸማቸውም በዕቅድ መመራት የነበረበት በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

36. የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የፅ/ቤት ግንባታውን ሥራ በሁለትም ዙር በሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በማጠናቀቅ ወደ ቴክኖሎጂ ገጠማው እንደሚገባ እንዳለበት እየታወቀ ጥቅምት 2002 ዓ.ም የሁለተኛው ዙር (2nd phase) የፅ/ቤት ግንባታውን ውል በተፈረመ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ የቴክኖሎጂውን ግባዓት አቅርቦትና የገጠማው ከሚያከናውነው የchina Poly group corporation Technologies Inc. ከተባለው ድርጅት ጋር የካቲት 2003 ዓ.ም የሁለተኛው ዙር (2nd phase) ውል ስምምነት መከናወኑ ኮርፖሬሽኑ ከመጀመሪያው ዙር የስራ ተሞክሮ በመነሳት የእርምት እርምጃ በመውሰድ የውል ስምምነቱ ማከናወኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የኮንትራት ዶክመንቶች መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የተገዙትን እቃዎች በመርከብና በአውሮፕላን ለማጓጓዝ፣ ለኢንሹራንስ፣ ለምድር ትራንስፖርት፣ እና ለጉምሩክ ቀረጥ የሚያፈልጉ ወጪዎች በቅድሚያ ለምን በጥናቱ ውስጥ እንዳልተካተቱ ምላሽ አልሰጡም፡፡

## ለፕሮጀክቶቹ የስራ ተቋራጮችንና አማካሪ ድርጅቶችን መረጣ በተመለከተ

37. ለማስፋፊያ እና ማሻሻያ ፕሮጀክትን የግንባታ እና የቁጥጥር ሥራ ላይ የሚሳተፉትን ተቋራጮች ሆነ አማካሪዎች የአገልግሎት ግዢው ሲከናወን በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ሊከናወን ይገባል። የአገልግሎት ግዢውን ያሸነፈው ድርጅትም ከኮርፖሬሽኑ (የቀድሞው ኢሬቴድ) ጋር የኮንትራት ውል ሊገባና ሥራውም በውሉ መሠረት ተፈጻሚ ሊደረግ ይገባል።

38. የቴክኖሎጂውን ግባዓት አቅርቦትና ገጠማ የስራ ተቋራጭ መረጣ በተመለከተ፡-

- ኮርፖሬሽኑ የቴክኖሎጂ ገጠማውን ሥራ ለማከናወን በተደረገው የጨረታ ሂደት በመጀመሪያ በ04/12/2001 በጸደቀ ቃለ ጉባኤ ላይ የቀረበው የፋይናንስ ዋጋ እና ቴክኒካል ግምገማ መሠረት አሸናፊው ተመርጦ የፐርፎርማንስ ቦንድ አስይዞ ውል ተፈራርሞ ሥራ ለመጀመር ባለመቅረቡ የጨረታ ውጤት ውድቅ ሆኖ ከአንድ አቅራቢ ዋጋውንም በድርድር እንዲፈጸም ለገ/ኢ/ል/ሚር ተጠይቆ በ18/02/2002 ዓ.ም ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተጻፈ ደብዳቤ በመፈቀዱ ብር 686,426,736.42 የሚያወጣ ስራን ከአንድ አቅራቢ ቻይና ፖሊ ቴክኖሎጂስ (china poly technologies inc.) ከተባለ ድርጅት ጋር በሁለት ደረጃ (ፌዝ) ተከፍሎ ዋጋውም በድርድር እንዲሰራ መደረጉ ታውቋል። ነገር ግን በግዥ መመሪያው ካሉት አማራጮች በድርድር ሥራውን ለማሠራት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተፈቀደለት መሆኑ ታውቋል። ነገር ግን ቻይና ፖሊ ቴክኖሎጂስ የቴክኒክ ብቃቱ የተሟላ መሆኑና የመንግስት ድርጅት ስለሆነ የሚል የጨረታ ኮሚቴው ያቀረበው ድፍን ያለ ምክንያት በስተቀር በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 694/2001 አንቀጽ 52.2 መሰረት ከሌሎች ተለይቶ ለምን እንደተመረጠና ድርድር የማድረጊያ አትኩሮተ-ነጥቦች ዝርዝር ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም።

39. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ የፕሮጀክቱ የመጀመሪያው ዙር ከምርጫ 2002 በፊት ደርሶ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ፕሮግራማቸውን ለመላው ህብረተሰቡ እንዲስተዋወቁ ስለተፈለገና ካለው ጊዜ አንጻር በጣም አስቸኳይ በመሆኑ በድርድር እንዲሰራ ታስቦ የተፈቀደ መሆኑን ገልጸዋል። ይሁን እንጂ የቻይና ፖሊ ቴክኖሎጂስ (chaina poly technologies inc) በምን አይነት መስፈርት እንደተመረጠ የሚያሳይ ዝርዝር መስፈርትና ድርድር የማድረጊያ አትኩሮተ-ነጥቦች ዝርዝር ሊቀርብ ባለመቻሉ የተሠጠውን መልስ መቀበል አዳጋች ያደርገዋል።

40. ግዢው ከአንድ አቅራቢ እንዲከናወን መደረጉ እና ዋጋው በድርድር መወሰኑ ለአሰራር ክፍተት ተጋላጭነቱ የሰፋ ሊያደርገው፣ እንደሚችልና መንግስት ሐብት እንዲባክን በር ሊከፍት ይችላል፡፡

41. የፅ/ቤት ግንባታ የስራ ተቋራጮችንና አማካሪ መረጣ በተመለከተ፡-

- በተጨማሪም በፕሮጀክቱ ሁለተኛው ዙር እንዲገነቡ ከታቀዱ ከ58 የጣቢያ ግንባታዎች ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጣቸው የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች የግዥ (የቅጥር ሂደት) በመንግስት የግዢ መመሪያ የተከተለ አለመሆኑ፡፡
- የኮንትራት አስተዳደርና ቁጥጥር ሂደትን በተመለከተ ደግሞ የቁጥጥር ስራውን ኮርፖሬሽኑ በራስ ሃይል ማስተዳዳር እንደሚችልና ለዚህም ፈቃድ እንዲሰጠው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና ለመንግስት ግዥ ኤጀንሲ በቀን 20 ጥር 2002 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ቁጥር ቴ02/611/33 እና ቴ02/680/6 በጠየቀው መሰረት በቀን 15/06/2002 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከመንግስት ግዥ ኤጀንሲ በቁጥር 12/3/54 በተጻፈ ደብዳቤ መፈቀዱን ከተደረጉ የደብዳቤ ልውውጦች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

42. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በመጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ የሁለተኛው ዙር የጽ/ቤት ግንባታዎች የቁጥጥር ስራውን በኮርፖሬሽኑ ባለሙያዎች ማከናወን እንደሚችል የመንግስት ግዥ ኤጀንሲ ተጠይቆ በመፍቀዱ ስራውን እንዳከናወኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

43. በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ የሁለተኛው ዙር የጽ/ቤት ግንባታዎች የቁጥጥር ስራው ኮርፖሬሽኑ ባለው በሁለት መሀንዲስ በመላው አገሪቱ የተሰራጩ 58 ፕሮጀክቶችን ክትትል ለማካሄድ መሞከሩ በባለሙያዎቹም ላይ ሆነ በሥራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

## የፕሮጀክት ማስፋፊያውንና የሽግግር ፕሮጀክቱን አፈጻጸም ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ

44. ድርጅቱ ለማስፋፊያ ፕሮጀክት ጨረታውን ካሸነፈ ድርጅት ጋር ውል ሊዋዋል ይገባል፡፡ በውሉ ላይም ሥራው ተጠናቆ የማስረከቢያ ጊዜ፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈጻጸም፣ የርክክብ ጊዜ የፍተሻ ስነ ስርዓት እና ዋስትናን በተመለከተ ኃላፊነትንና ግዴታን በግልጽ ያስቀመጠ ሊሆን ይገባል፡፡ በግንባታ ሳይቶች ላይ ለሚኖሩ የጥራት ቁጥጥር፤ የዲዛይን

መጣጣምና ሱፐርቪዥን ስራው በተቀመጠለት መስፈርት መሰረት መከናወኑን በአማካሪ መሀንዲስ ሊረጋገጥ ይገባዋል፡፡ የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴ በየደረጃው ለመከታተል የሚያስችል የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

45. በፕሮጀክቱ የመጀመሪያው ዙር ጣቢያዎች ግንባታን በተመለከተ ከ19 ውስጥ የ16ቱ ጣቢያዎች አጠቃላይ ስራ ተጠናቆ ሐምሌ 2003 ዓ.ም የመጨረሻ ርክክብ የተፈፀመ ሲሆን የሶስት ጣቢያዎች (ደሴ፣ ፊቼና ንፋስ መውጫ) ግንባታዎች ሙሉ በሙሉ ባለመጠናቀቃቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ርክክብ አለመፈጸሙና በሦስት ዓመት መዘግየቱን ከአፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል ዝርዝር የጣቢያዎቹን ስም በአባሪ 4 ተያይዞል፡፡

46. በተጨማሪም በፕሮጀክቱ ሁለተኛው ዙር እንዲገነቡ ከታቀዱ 58 የጣቢያዎች ግንባታዎች ከጥቅምት 2002 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2004 ዓ.ም ተጠናቆ ርክክብ እንደሚፈጸም በኮንትራ ውሉ ቢቀመጥም፡፡ ከዚህ ውስጥ የ27ቱ ጣቢያዎች አጠቃላይ ስራ ተጠናቆ ከሰኔ 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 2006 ዓ.ም የመጨረሻ ርክክብ የተፈፀመ ሲሆን በ 31 ጣቢያዎች በቃሊቲ የኮንስትራክሽን ውጤቶች ማምረቻ ድርጅት 20፣ በሌሊሳ ገልሜሳ የህንጻ ተቋራጭ 4፤ በነጋሽ አካል የህንጻ ተቋራጭ 3፤ በአዳነ ተሰማ የህንጻ ተቋራጭ 4 የተከናወኑ ግንባታዎች ሙሉ በሙሉ ባለመጠናቀቃቸው ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ የጣቢያዎች ርክክብ አለመከናወኑና በሁለት ዓመት መዘግየቱን ከአፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል ዝርዝር የጣቢያዎቹን ስም አባሪ 5 ይመልከቱ፡፡

47. ከዚህም ባሻገር የቴክኖሎጂ ግንባታቸው ተጠናቀው ርክክብ ከተፈጸመባቸው በናዝሬት፤ ድሬደዋ፤ ደሴ፤ ወልዲያ፤ ባህር ዳር፤ ጮቄ፤ ፊቼ እና አክስታ ማሰራጫ ጣቢያዎች መስጠት ያለባቸውን አገልግሎት መስጠት ሳይችሉ የተበላሹ Generator፣ control unit፣ AC[6]፤ AVR[7] እና Exciter[8] ሲሆኑ በተጨማሪም ድሬደዋ፤ ደሴ፤ ወልዲያ፤ ባህር ዳር፤ ጮቄ፤ ፊቼ እና አመንቲላ ማሰራጫ ጣቢያዎች ላይ ደግሞ UPS[9] የሚባለው መሳሪያ አለመኖሩ በመስክ ጉብኝት እና ከሰርቬይ ከተሰጠው መልስ ለማወቅ ተችላል፡፡

---

6 Air Conditioner

7 Automatic Voltage Regulator

8 Exciter/ ኤክሳይተር/- በስርጭት ሂደት ውስጥ ብዙ ስራዎች የሚከናወንበት የማሰራጫ መሳሪያ

9 Uninterruptible Power Supply

48. ስለ ጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የስራ ሂደታቸውን በተገቢው ጊዜ አጠናቀው የመጨረሻ ርክክብ የተከናወነላቸው ግንባታዎች አጠቃላይ ሁኔታን ስንመለከት በማንኛውም ግንባታዎች ላይ ሊከሰት ከሚችሉ ጥቃቅን ችግሮች ውጪ በጥሩ ይዞታ የሚገኙ ሲሆን ይህንኑ ሂደት ያላጠናቀቁ የተወሰኑ ፕሮጀክቶች ላይ የሚታዩ ችግሮች ተለይተው ከመጀመሪያው ዙር የደሴና የፊቼ ጣቢያዎች ለተቋራጭ ድርጅቶች ተደጋጋሚ ማሳሳቢያና ማስጠንቀቂያ የተሰጠና ጉዳዩ ህግ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በሁለተኛው ዙር ከቃሊቲ ኮንስትራክሽን ጋር በጥቅል ውለታ የተገባባቸው 20 ጣቢያዎች ቀሪ ስራዎች እንዲጠናቀቁና እርክክብ እንዲፈጸም በተደጋጋሚ ሙከራ ቢደረግም እስከአሁንም ድረስ ምንም አይነት ምላሽ ማግኘት አለመቻሉና በሌሎች 3 የግል ተቋሯጮች ይከናወን የነበረው ስራ አጠቃላይ የእርምት ስራ ተጠናቆ ለርክክብ በሂደት ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

49. ከዚህም ባሻገር ስለ ጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቃለ መጠይቅ በመውጫ ስብሰባ ወቅትና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ፕሮጀክቱ ሰፊ መሆንና በመላ ሀገሪቱ ተበታትኖ የሚከናወን ስራ በመሆኑ በሁለት ባለሙያ ክትትልና ቁጥጥር የማድረጉ የስራ ሂደት ላይ ተጽኖ በማሳደሩ ምክንያት 58ቱም የጽ/ቤት ግንባታዎች ለመከታተል አስቸጋሪ በመሆኑና ኮርፖሬሽኑ ካለው የሰው ኃይል ጋር ስለማይመጣጠን የክትትልና ቁጥጥር ስራውን በተመረጡ የዋና ዋና በሚባሉ የግንባታ ስራ ዘርፎች ላይ ብቻ እንድንገኝ ያስገደደ በመሆኑ በግንባታው የስራ ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽኖ እንደሚፈጥርና የሪፖርት ምልልሱም ቢሆን የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴ በየደረጃው ለመከታተል የሚያስችል የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡ ከየማሰራጫ ጣቢያዎቹ ተነቅለው የተወሰዱትን መሣሪያዎች በተመለከተ ተገጥመው ሥራ ከጀመሩ በኋላ በማዕከል በዋናው መስሪያ ቤት ስቱዲዮዎችና በፉሪ ማሰራጫ ጣቢያ ያሉት መሣሪያዎች ስለተበላሹና ባለው የኃይል መቆራረጥ ምክንያት እና ለኢዲዮው አርካይቭ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ግዥ በመዘግየቱ በአንጻራዊነት ለማሰራጫ ጣቢዎቹ ተነቅለው እንዲመጡና ሲገዙ እንዲመለሱ ለማድረግ በወቅቱ በመመረጡ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

50. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ Generator፣ control unit፣ AC፤ AVR፤ Exciter እና UPS የሚባሉት መሳሪያዎች መበላሸትና በጣቢያዎች ከተገጠሙ በኃላ ተነቅለው በተለያዩ ጊዜያት ወደ ዋናው መስሪያ ቤት እንደተወሰዱ እና ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መሣሪያዎቹ ወደ ጣቢያዎቹ እንዳልተመለሱ ከተከለሱ ሰነዶችና በመስክ ጉብኝት ለመረዳት በመቻሉ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

51. ሁለተኛው ዙር የጽ/ቤት ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክቶች በየደረጃው የተሰሩ ስራዎች በተቀመጠላቸው ዲዛይን እና እስፔሲፊኬሽን መሰረት ሳይሆን በተመረጡ የዋና ዋና በሚባሉ የግንባታ ስራ ዘርፎች ላይ ብቻ በመከናወናቸው የቁጥጥርና የክትትል ሰራው ሙሉ በሙሉ በተቆጣጣሪ መሃንዲስ አለመረጋገጡ፤

52. የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ግምገማ የሚከናወነው ቁፋሮ፤ ኮንክሪት ሙሌት እንዲሁም የግንባታ ግባዓቶችን በተመለከተ በድርጅቱ ማሀንዲሶች ቁጥጥሩ የተከናወነ ሲሆን፤ የታወር ግንባታውን በተመለከተ ደግሞ የማቴሪያል አቅርቦትንም ሆነ ግንባታውን መሳሪያውን ለማቅረብና ለመትከል ባሸነፈው በራሱ በቻይናው ኮንትራክተር አማካኝነት እንዳተከናወነ ለመገንዘብ ተችላል፡፡

53. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ለቃለመጠይቅ፣ ለነባረዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት መልስ በሁለተኛ ዙር ለተከናወኑ ፕሮጀክቶች በመጠንም ሆነ በውስብስብነት ደረጃ ሲታዩ አነስተኛ ከመሆናቸው አንጻር የቁጥጥሩንም ሂደት በተወሰነ የስራ ዓይነቶች ላይ የሚወሰን በመሆኑ፣32 ፕሮጀክቶች ደግሞ የመከላከያ ኮንስትራክሽን ሙሉ ኃለፊነቱን ወስዶ እንዲሰራቸው በመደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ስራዎቹ በተለያየ ቦታ ከመበታተናቸውና ከፕሮጀክቶች ብዛት አኳያ የተወሰኑ ክፍተቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የግንባታውን ትልቁን ድርሻ የሚዘውን የታወር መሰረት ግንባታን ቁጥጥርን በተመለከተ ለራሱ ለኮንትራክተሩ የተተወ በመሆኑ፣ ከመከላከያ ኮንስትራክሽን ጋር የተገባውም ውልም የቁጥጥር ሥራውን በተጨማሪ ለማከናወን ስለማያካተትተና የተወሰኑት ፕሮጀክቶችም በተባለላቸው ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ተከናውኗል ለማለት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## የ24 ሰዓት የሥርጭት ሽፋን ማዳረስንና አማራጭ ቻናሎችን መጀመር ተመለከተ

54. የማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ የፕሮግራም ስርጭት የአየር ሰዓት ውስንነትን ችግር ሊፈታ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቴሌቭዥን አማራጭ ቻናሎች ተከፍተው ሥራ ሊጀምሩ ይገባል፡፡

55. በማስፋፊያና ማሻሻያ ኘሮጀክቱ የ24 ሰዓት የሥርጭት ሽፋን ታሳቢ ተደርጐ በሁሉም ክልሎች የቴሌቪዥን ማሠራጫ ጣቢያዎች እንዲገነቡ፣ በድርጅቱ የሚታዩ ጉልህ የሆኑ ችግሮችን በተለይም የስርጭት አድማስ ውስንነት፣ የፕሮግራም ስርጭት ጥራት ጉድለትን

ለመቅረፍ የሚል በኮርፖሬሽኑ (የቀድሞው ኢሬቴድ) ለፕሮጀክቱ በፀደቀ የጥናት ፕሮፖዛልና በ5 ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ተይዟል፡፡

56. ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት በ11 ማሰራጫ ጣቢያዎች (ጂንካ፣ ሀርገሌ፣ ፊቅ፣ ማጂ፣ ዲቾቶ፣ ጮቄ ተራራ፣ አዲረመፅ፣ ዋርደር፣ ቀብሪደሃር፣ አዳባ ዲንሾ፣ ጉባ እና ጉዴ የማሠራጫ ጣቢያዎች) በየሳምንቱ ከሰኞ እስከ አርብ ከቀኑ 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4፡00 ቅዳሜ እና እሁድ ደግሞ ከቀኑ 7፡00 እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት ብቻ ስርጭት እያከናወኑ መሆናቸው፣ ለጣቢያዎቹ የኤሌክትሪክ ኃይል መዘርጋት የፕሮጀክቱ አካል ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ አለመዘርጋቱን በመስክ ጉብኝት እና ከኮርፖሬሽኑ የዕቅድ ክንውን ዓመታዊ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ስለሁኔታው የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ለየጣቢያዎቹ የኤሌክትሪክ መስመር ስላልተዘረጋላቸውና ይህንን ችግር ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ጋር ችግሩን ለመፍታት ተደጋገሚ ጥረት ቢደረግም ችግሩን መቅረፍ ባለመቻሉ ምክንያት አጫጭርና የተቆራረጠ ሥርጭትን ለመጠባበቂያነት በተተከሉት ጄነሬተሮች እየተጠቀሙ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

58. ይህ በመሆኑ ጣቢያዎች ላይ በሚደርሰው ተደጋጋሚ የሃይል መቆራረጥ ምክንያት ጣቢያዎቹ የ24 ሰዓት አገልግሎት መስጠት አለመቻል፤ ጀነሬተሮቹ በቀን ማገልገል ከሚገባቸው ሰዓት በላይ እየሰሩ በመሆኑ ለመጡበት አላማ ባለመዋላቸው ጀነሬተሮቹ እድሜቸውን ከማሳጠሩም በላይ የተገጠመውን የትራንስሚሽንና የኤሌክቶሮኒክ ዕቃዎች በተደጋጋሚ እየተበላሹ መሆንና ከፍተኛ የሆነ ብልሽት እየደረሰባቸው በመሆኑ ኮርፖሬሽኑን ተገቢ ላልሆነ ወጪ ዳርጎታል፡፡

59. በቀድሞው (በኢ.ሬ.ቴ.ድ) እየተገነባ ያለው ሀገርአቀፍ ኔትወርክ የተደራሽነት አድማስ ከፍተኛ መሆን፣ በሀገርአቀፍ ደረጃ የተመረጠው DVB-T2 ስታንዳርድ 22 ፕሮግራም የማስተናገድ አቅሙ እና በሀገራችን አሁን ያሉትን የብሮድካስተሮች ብዛት ከግምት ውስጥ ሲገባ አንድ ሀገራዊ የጋራ ሄድ-ኢንድ (Head End) መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ የዲጂታል ቴሬስቴሪያል ቴሌቪዥን ቴክኖሎጂ ሽግግር ፍኖተ ካርታ (ሮድማፕ) ሰነዱ ቢገልጽም ኮርፖሬሽኑም በ2005 ዓ.ም የዲጂታል ስርጭትን በማስጀመርና አሁን ያለውን የቴሌቪዥን ቻናል ብዛት ከስምንት (8) በላይ በማድረስ ለድርጅቱ፤ ለግል ተቋማትና ለክልል መንግስታት በቂ የአየር ሰዓት መመደብና አገልግሎት የሚሰጥባቸውን ቋንቋዎች ማሣደግ የሚያስችል መሰረተ ልማት መገንባት በሚል ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን ኦዲቱ

እስከተጠናቀቀበት ድረስ የቴሌቭዥን አማራጭ ቻናሎች ማሳደግ ያልተቻለ መሆኑንና ዕቅዱ አለመሳካቱ ከኮርፖሬሽኑ የዕቅድ ክንውን ዓመታዊ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. ይህን በተመለከተ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ የቴሌቭዥን አማራጭ ቻናሎች ማሳደግ ያልተቻለበት ምክንያት DVB-T2 የተርስቴሪል ሲስተም ግዥን ለመፈጸም ጨረታ ከወጣ ቦኃላ ተሳታፊ የሆኑ ኩባንያዎች ለግዥው ማስፈጸሚ የሚሆን የንግድ ብድር (commercial loan) ለማመቻቸት ባቀረቡዋቸው ውሎች የቻይና ኩባንያዎች የተሸሉ ሆነው ቢገኙም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከቻይና ባንኮች የሚገኘው ብድር ውስን መሆኑንና ቅድሚያ ለትላልቅ ፕሮጀክቶች (Mega Projects) የሚውል በመሆኑ ሌላ አማራጭ እንድንፈልግ በቁጥር ሕ/አ/5/77 በ15/02/2006 በተጻፈ ደብዳቤ ማሳወቁን ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም በፋይናስ አቅርቦት፤ አቅም ያላገናዘበ ዕቅድ እና የማስፈጸም አቅም ችግሮች ጋር በተያያዘ የዲጅታል ሽግግሩ ባለመተግበሩ ዕቅዱ ማሳካት እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡

61. የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ የፕሮጀክቱ ጥናትና የስትራቴጂክ ዕቅድ መዘጋጀቱ ፕሮጀክቱን በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ ባለመደረጉ ኮርፖሬሽኑ የታሰቡት አማራጭ የቴሌቭዥን ቻናሎች እንዳይኖሩ አድርጎታል፡፡

## ዘመናዊ አርካይቭ ስርዓትና ዳታቤዝ አደረጃጀትን በተመለከተ

62. በማስፋፊያ እና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ ዘመናዊ የኔትዎርክ አርካይቭና ኤዲቲንግ ስርዓት ሊዘረጋ፤ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ኦንላይን የሚተላለፉና የተላለፉ ዳታዎችን በዘመናዊ መንገድ የሚያስቀምጥ ዳታ ቤዝ ሊገነባና የኮርፖሬሽን የፕሮዳክሽን ስራዎች ደህንነታቸው በመጠበቅ እንዲከማቹና በክምችት ክፍል የሚገኙ ግብዓቶች በቀላሉ የገቢ ምንጭና የፕሮዳክሽን ግብዓት ሊሆኑ በሚችሉበት ሁኔታ ተደራጅተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡

63. ዘመናዊ የኔትዎርክ አርካይቭና ኤዲቲንግ ስርዓት በመዘርጋት የፕሮዳክሽን ስራዎች ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ በፍጥነትና በጥራት እንዲከናወኑ ማድረግ በክምችት ክፍላችን የሚገኙ ግባዓቶች በቀላሉ የገቢ ምንጭና የፕሮዳክሽን ግብዓት እንዲሆኑ ማስቻል የሚል በስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ የታቀደ ቢሆንም፤

64. የአርካይቭ ስርዓት ዲጂታላይዝ ማድረግ ስራ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም በጀት ዓመት በየዓመቱ ይተገበራል ተብሎ በዕቅድ ቢያዝም የትግበራው ስራ ግን እስከ ሰኔ 2006 ዓ.ም ያልተጀመረ መሆኑን፤

65. በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን የሚተላለፉና የተላለፉ ዳታዎችን በዘመናዊ መንገድ የሚያስቀምጥ የመረጃ ቋት /Database/ በማዕከል ደረጃ ያልተዘጋጀና ተግባራዊ የሚደረግበት ስርዓት አለመኖሩን፤

66. ይህ በተመለከተ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቃለ መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ በአሁኑ ሰዓት የመሣሪያ ግዥና ተከላ ተከናውኖ ሥራ የጀመረ መሆኑን ገልጸዋል። ነገር ግን የቴሌቪዥን አንድ መቶ ሺህ ሰዓት (100,000 ሰዓት) እና የሬድዮ ሰማኒያ ሺህ ሰዓት (80,000 ሰዓት) የአናሎግ አርካይቭ ያሉት በመሆኑ እነዚህን የመገልበጡ ሥራ ረጅም ጊዜ የሚወስድ መሆኑን ገልጸዋል።

67. በኮርፖሬሽኑ አርካይቭ ውስጥ ያሉ የማቴሪያሎች ወጪና ገቢ በሚደረጉበት ወቅት የሚደረገው ቁጥጥር የዘመኑ ቴክኖሎጂ የማይጠቀሙ በመሆኑ፣ ቁጥጥር ስራው ላይ በቂ የሰው ኃይል አለመመደቡ፣ የአርካይቭ ማቴሪያሎች እጅግ ብዛት ያላቸው ቢሆንም ተገቢ የሆነ የቁጥጥር ስልት አለመቀየሱ፣ እንዲሁም ድርጅቱ ከፍተኛ የድምፅና ምስል ክምችት ያለውና ሌሎች ድርጅቶች የሌላቸው የፕሮዳክሽን ግብዓት ክምችት ያለው በመሆኑ ተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑን ከቀረቡት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል።

68. ይህ በተመለከተ የኮርፖሬሽኑ የስራ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ኦዲዮ ቪዥዋል ላይብረሪ ከተለያዩ የመቅረጫ ካሴቶች ላይ ወደ ዲጂታል ሲስተም መለወጥ የተጀመረው በያዝነው በጀት ዓመት መጀመሪያ (ከሐምሌ 26 ቀን 2006 ዓ.ም) ከዕቅዱ ከተመለከተው በአራት ዓመት በመዘግየት ሲሆን፤ በሬዲዮ ኦዲዮ በኩል በሲዲ ላይ ያሉ ዘፈኖች ወደ ዲጂታል ሲስተም የተቀየሩ ቢሆንም ዳታው በእንግሊዘኛ የገባና የአማርኛ ሶፍትዌር ባለመሆኑ በቀጥታ ስርጭት ወቅት የሚፈገውን መረጃ በተፈለገው ፍጥነት ለማግኘት አዳጋች አድርጎታል።

69. የዲጅታል ስራው ባለመጠናቀቁና የፕሮዳክሽን ስራዎች ሙሉ በሙሉ ገቢ አለመነጨም ባይባልም በሚፈለገውና በሚጠበቀው መልኩ አለመሆኑ ድርጅቱን ሊሰበስብ የሚችለውን ገቢ እንዳይሰበስብ አድርጎታል፡፡

